**በደቡብ አፍሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ድጋፍ ሰጪ**
Kinijit Support group of South Africa

# ከደቡብ አፍሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ድጋፍ ሰጪ አካል የተሰጠ የአዲስ ዓመት የመልካም ምኞት መግለጫ!

ለአገራች እድገት፡ ለህዝባችን እኩልነትና ዘላቂ ሰላም ለማስፈን በግንቦት 7 1997 ቱ ታሪካዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎቱና ይሁንታውን በፈቃዱ ቢገልጥም በወያኔ አምባ ገነናዊና አሻፈረኝ ባይነት የዜግነትና ሰብአዊ መብቱን ተረግጦ በጨካኞች ጥይት መቆላቱ፡ መደብደቡና ለእስር መዳረጉ የትላንት ትዝታ ብቻ ሳይሆን ዛሬም በመከራ አረንቋ ውስጥ መዳከሩ አለም ያወቀው ገሃድ ሚስጢር ሆኗል፡፡

ትላንት ለህዝባቸው አዲስ የተሰፋ ብርሃን ለመፈንጠቅ በህዝባቸው ልብ ውስጥ በመናኘት በምርጫ ድል የመቱት እውነተኛና ቆራጥ መሪዎቻችን *ሲያሻኝ ጭስ ወጋኝ* የሚለው የኢህአዴግ መንግስት ያለ ጥፋታቸው አግባብ ባልሆነ እስር ቢያንገላታቸው አካላቸው ቢከሳና ቢጠቁርም አላማቸው ፅኑ በመሆኑ መንፈሳቸው ከምንግዜውም በላይ በርትቶ እንደሚገኝ በአዲስ ዓመት የመልካም ምኞት መልዕክታቸው ላይ ገልጠውልናል፡፡

በኢትዮጵያ እኩልነትንና ሰላምን ለማስፈን የዴሞክራሲን ብርሃን ከፍ አድርጎ ለማበራትና የኢህአዴግ መንግስት ያቀደውን የመጨረሻ ዕኩይ ዕቅድ ለማኮላሸት ከጎጥና ከዘር የፖለቲካ አመለካከት በፀዳ አገር አቀፋዊና ብሔራዊ ትግል የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘን ይህንን የታሪክ አጋጣሚ የጣለብንን ዕዳ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀየር የግድ ይለናል፡፡

ስለሆነም እኛ በደቡብ አፍሪካ የምንገኝ የደቡብ አፍሪካ የቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ድጋፍ ሰጪ አካል በእስር ላይ ለሚገኙት መሪዎቻችን ያለንን አክብሮትና አድንቆት እየገለፅን ከቅንጅት አለም አቀፍ አመራር ጎን በመሰለፍ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል በድጋሚ ቃል እየገባን መጪው አመት ለአገራችንና ለህዝባችን የዴሞክራሲ፡ የነፃነት፡ የሰላምና የዕድገት ይሆን ዘንድ ምኞታችንን እንገልፃለን፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ**

**217 ጂ.ፒ ስትሪት3ኛ ፎቅ ናዲባ ሕንፃ ጆሃንስበርግ ደቡብ አፍሪካ**
**ስልክ ቁጥር 27723498980 27723115306** e-mail kinijitsa@yahoo.co.uk